*የስብሰባው ዓይነት፡ የሀብት ማሰባሰብ ፕሮግራም*
*ቀን፡ ሚያዝያ 20፣ 2011*
*ቦታ፡ ሳፋየር ሆቴል*

*የተከበራችሁ የነጻነትና እኩልነት ፓርቲ አባላትና ደጋፊዎች*

*የተከበራችሁ የፖለቲካ ፓርቲዎች ተወካዮች*

*ክቡራትና ክቡራን፣*

**ድጋፍ ለነጻነት፣ ለእኩልነትና ለፍትህ** በሚል መሪ ቃል **ለነጻነትና እኩልነት ፓርቲ** ድጋፍ ለማሰባሰብ በተዘጋጀው ፕሮግራም ላይ ጥሪያችንን አክብራችሁ ስለተገኛችሁ በራሴ እና በመላው የፓርቲያችን አባላት ስም ከፍ ያለ ምስጋና አቀርባለሁ፡፡

**ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ** አዲስ የፖለቲካ ፓርቲ ነው፡፡ አላማው ሀገራችንን ከሁለት ዋና ዋና ታሪካዊ ጠላቶቿ ነጻ ማውጣት ነው፣ **ከድህነት እና ኢ-ፍትሀዊነት**፡፡ አዲሱ ፓርቲ ለሀገራችን ዘመን ተሻጋሪ ችግሮች አዳዲስ ሀሳቦችና መፍትሄዎችን በማመንጨት ኢትዮጵያን አስረው ከያዟት ችግሮች ማላቀቅ ነው፡፡

ላለፉት አስርት አመታት በሀገራችን የተፈጠሩ ድርብርብ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ ሁነቶች በተለይም ባለፈው ሩብ ምእተ አመት የታዩ ለውጦች ሀገራችንን መንታ መንገድ ላይ እንድትቆም አድርጓታል፡፡ ከሁለቱ መንገዶች አንደኛው የመቻቻል፣ የአንድነት፣ የአብሮነት የሰላም እና የወንድማማችነት መንገድ ነው፡፡ ይህ መንገድ አብዛኛው ኢትዮጵያዊ የሚመኘውና ማየት የሚፈልገው መንገድ ሲሆን የረዥም ዘመን በሰላም አብሮ የመኖር ታሪክ ያላቸው የሀገራችን ህዝቦች በዘላቂነት በፍቅርና በመከባበር ወደ ሚኖሩባት ሀገር ያደርሳል፡፡ ይህ መንገድ የእድገት እና የብልጽግና መንገድ ሲሆን ሁሉም ኢትዮጵያዊ በነጻነትና በእኩልነት ወደሚኖርባት የበለጸገች ሀገር ይወስዳል፡፡

ሁለተኛው መንገድ የልዩነት፣ የጥላቻ፣ የመከፋፈል መንገድ ነው፡፡ ይህ መንገድ የሞት፣ የርሀብ፣ የስደት፣ የበቀል፣ መንገድ ሲሆን በዚህ የጥፋት መንገድ ላይ መጓዝ የሚፈልግ እውነተኛ እና ሀገር ወዳድ ኢትዮጵያዊ አይኖርም፡፡ ምክንያቱም ይህ መንገድ መጨረሻው አሸናፊ ወደ ሌለው የእርስ በእርስ እልቂት እና መበታተን የሚወስድ መንገድ ስለሆነ፡፡ **ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ** ሀገራችን ወደ አንድነት፣ ወደ ሰላምና ወደ እድገት በሚወስደው ጎዳና ተጉዛ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ፍትህ የሰፈነባት፣ ዜጎች በነጻነት፣ በእኩልነትና በፍትህ የሚኖሩባት፣ እውነተኛ መቻቻል እውን የሆነባት፣ የብሄር፣ የቋንቋ የባህል ልዩነቶች የሚከበሩባ ሀገር እንድትሆን የሚሰራ ፓርቲ ነው፡፡ **ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ** አብሮ በማሸነፍ መርህ ከማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ ወይም ሀይል ጋር ለመስራት ዝግጁ የሆነ ከየትኛውም ጽንፈኛ አስተሳሰብ ጋር የማይወግን፣ በመግባባትና በድርድር የሚያምን ፓርቲ ሲሆን ይህም ለአብዛኛው ኢትዮጵያዊ ተመራጭ የፖለቲካ ፓርቲ እንዲሆንና በአጭር ግዜ ውስጥ በሀገራችን ከሚኖሩ ጠንካራ ፓርቲዎች ውስጥ አንዱ እንዲሆን ያደርገዋል፡፡

**ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ** ለብዙ አስርተ አመታት በአባላቱ ልብ ውስጥ ተቀምጦ ለመወለድ አመቺ ግዜ ሲጠብቅ ከቆየ በኃላ ከአለፈው አንድ አመት ጀምሮ ሀገራችን ውስጥ በተፈጠረው የተሻለ የፖለቲካ ስርአት እውን የሆነ ፓርቲ ነው፡፡ **ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ** መሰረቱ እና ግቡ ፍትህ ነው፡፡ ፍትህ በብሄሮች በካከል፣ በጾታ መካከል፣ በትውልድ መካከል፣ ፍትህ በከተማ እና ገጠር መካከል፣ በመደቦች መካከል፣ በአርብቶ አደር፣ በአርሶ አደር እና በላብ አደሩ መካከል፡፡

**ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ** ሰው መሆን ከምንም ነገር በላይ ነው ብሎ የሚያምን ማንኛውም ኢትዮጵያዊ በሀገሩ ውስጥ በፈለገው አካባቢ ሰርቶ የመኖር መብቱ እንደረጋገጥ የሚሰራ ፓርቲ ነው፡፡ **ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ** ሁሉንም የሀገራችን ብሄረሰቦች፣ ቋንቋ፣ ባህል እና እምነት በእኩልነት የሚመለከት፣ አንዱን አወድሶ ሌላውን የማያኮስስ፣ ለአንድነት ዘብ የሚቆም፣ ለብዝሀነት የሚታትር ፓርቲ ነው፡፡

**የተከበራችሁ የፕሮግራሙ ተሳታፊዎች**

መላው የሀገራችን ህዝቦችና ዓለም በግልጽ እንደሚያውቀው በአሁኑ ወቅት ሀገራችን በከፍተኛ ችግር ውስጥ ትገኛለች፡፡ ኢትዮጵያ ከአለም እጅግ ድሀ ሀገሮች መካከል ሶስተኛ ስትሆን ከግማሽ በላይ የሀገራችን ህዝብ ከድህነት ወለል በታች ኖራል፡፡ ከ23 ቢሊየን ዶላር በላይ የውጭ እዳ ጫና ያለባት ኢትዮጵያ ለአንድ ወር ግዥ ለመፈጸም የሚያስችል የውጭ ምንዛሬ እንኳ የላትም፡፡ ስራ አጥነት በታሪክ ከፍተኛ ላይ ደርሷል፡፡ ኢኮኖሚያችን በእጅጉ ተቀዛቅዟል፡፡ ልጓም የጠፋለት የዋጋ ግሽበት የዜጎቻችንን የኑሮ ሁኔታ ከግዜ ወደ ግዜ እንዲያሽቆለቁል አድርጎታል፡፡

ሀገሪቱን የሚያስተዳድራት ገዥው ፓርቲ በርእዮተ-ዓለም፣ በአስተሳሰብ፣ በአደረጃጀትና በአተገባበር እጅግ እንደተዳከማ ራሱ ፓርቲው ይመሰክራል፡፡ የተፎካካሪ ፓርቲዎችም ከገዥው ፓርቲ ባልተናነሰ ሁኔታ አቅማቸው ውስን የሆነበት ዘመን ላይ እንገኛለን፡፡ ዙሪያ ገደል የሆነበት የሀገራችን ህዝብ ከዚህ አጣብቂኝ ለመውጣት አዲስ ኃይል፣ አዲስ አመለካከት፣ የጠራ የፖለቲካ መስመር፣ አዳዲስ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች ያለው የፖለቲካ ድርጅት በሚፈልግበት በአሁኑ ወቅት **ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ** በሀገራችን የፖለቲካ ሜዳ ውስጥ ገብቷል፡፡ **ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ** እና አባሎቹ ረዥም እና ውስብስ ጉዞ ከፊታችን ይጠብቀናል፡፡ ይህንን እጅግ ከባድ ኃላፊነት በተሳካ ሁኔታ ለመወጣት ትልቅ መስዋእትነት ለመክፈል ከመቸውም በበለጠ ልንዘጋጅ ይገባል፡፡ምክንያቱም ለሀገርና ለህዝብ የሚከፈል መስዋእትነት ድርጅታዊ ግዴታ ከመሆኑም ባሻገር የተቀደሰ ተግባር ነውና፡፡

**ውድ የነጻነትና እኩልነት አባላት እና ደጋፊዎች**

ይህንን ፕሮግራም በምናካሂድበት በአሁኑ ሰአት በሚልዮን የሚቆጠሩ ዜጎቻችን ከቤት ንብረታቸው ተፈናቅለው የእለት ጉርስ ማግኘት ሳይችሉ በባዶ ሆድ በርሀብ ይሰቃያሉ፡፡ ከነዚህ ውስጥ አብዛኞቹ ጨቅላ ህጻናትና አቅመ ደካማ አረጋውያን መሆናቸውን ስናስብ ሀዘናችንን ድርብ ይሆናል፡፡ ዛሬ እኛ በዚህ የስብሰባ አዳራሽ ውስጥ ተገኝተን ስለ

ሀገራችን መጻኢ እድል ስንመክር በሙቶ ሺዎች ወይም ከዚያ በላይ ዜጎቻችን በቀላል ህክምና ሊድኑ በሚችሉ የእድሜ ልክ በሽታዎች እየተሰቃዩ የወገን ያለህ ይላሉ፡፡ በአስር ሺዎች የሚቆጠሩ ነፍሰ ጡሮች በወሊድ ምክንያት ህይወታቸው ያልፋል፡፡ ከፍተኛ ቁጥር  ያላቸው ወገኖቻችን የመልካም አስተዳደር እና የፍትህ እጦት ሰለባ ሆነው የመከራ ህይወት ይገፋሉ፡፡ በሙቶ ሺህ የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን ህይወታቸውን በጎዳና ላይ መስርተው ዝናብና ሀሩር፣ ብርድና ሙቀት፣ ክረምትና በጋ እየተፈራረቀባቸው የተሻለ ነገን እያለሙ ይኖራሉ፡፡ከነዚህ ውስጥ ጥቂት ያማይሆኑት ሴቶች መሆናቸውንና የሚደርስባቸውን ድርብርብ ስቃይ ስናስብ ኃላፊነታችን እጅግ እጅግ ከፍተኛ መሆኑን እናያለን፡፡

ከላይ የተመለከቱት ድርብርብ ችግሮችና ፈተናዎች ልዩ ልዩ መንስኤዎች ቢኖሯቸውም የችግሮቹ መሰረታዊ ምንጭ አንድ እና አንድ ነው፡፡ኃላፊነትና ሰብአዊነት፣ ለህዝብ የሚወግን፣ የህዝብን ሰቆቃ እና ሮሮ እያየ እንቅልፍ የማይተኛ፣ የሀገር እና የህዝብ ክብር የሚያስቀድም፣ ከጉቦ እና አድሏዊ አሰራር የጸዳ፣ ከወገንተኝነት የራቀ የፖለቲካ አመራር እጦት ነው፡፡

**ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ** በሀገራችንና በዜጎቻችን ላይ የተጫነውን ተቆጥሮ የማያበቃ ችግር እና ሰቆቃ ለመታደግ እና የምንወዳትን ሀገር እና የህዝባችን ጥሪ መልስ ለመስጠ ለአንድ አላማ የተሰባሱ ዜጎች ውጤት ሲሆን ሀገራችንን አስረው ከያዟት ችግሮችና መሰናክሎች ሊታደጋት አንድ ብሎ ትግል ጀምሯል፡፡ **የነጻነትና እኩልነት ፓርቲ** አባላት በሀገር ጉዳይ ላይ ዳር ተቀምጦ ከመተቸትና አስተያየት ከመስጠት ወጥተን ቀጥተኛ ተዋናይ ለመሆን ሜዳ ውስጥ ገብተናል፡፡ሀገራችን ከጎዳት የ"**እኔ ምንአገባኝ**" አስተሳሰብ ወጥተን እኔ እያለሁ ሀገሬ እንዴት ድሀ ትሆናለች ብለን የድርሻችንን ለመወጣት ትግል ጀምረናል፡፡

ፓርቲያችን ራእዩን እውን ለማድረግ ሲንቀሳቀስ ልዩ ልዩ ግብአቶች የሚያስፈልጉት ሲሆን የሰው ኃይል እና ገንዘብ ዋነኛዎቹ ናቸው፡፡የፖለቲካ ስራን አስቸጋሪ ከሚያደርጉት ባህሪያት አንዱ ከፍተኛ ወጪ ያለው መሆኑ ነው፡፡ችግሩን ይበልጥ የሚያባብሰው ደግሞ የፖለቲካ ፓርቲዎች የገንዘብ ምንጭ የተወሰኑ መሆናቸው ነው፡ በሀገራችን ህግ መሰረት የፖለቲካ ፓርቲዎች የገቢ ምንጮች ከአባላት የሚሰበሰብ የአባልነት ክፍያ እና ከኢትዮጵያውያን ብቻ የሚገኝ የገንዘብ ድጋፍ ሲሆን በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ገቢ ሊያስገኝ በሚችል ማናቸውም ስራ ላይ መሰማራት አይችሉም፡፡ እነዚህ እውነታዎች የፖለቲካ ፓርቲዎች አስተማማኝ ድጋፍ የሚያገኙበትን ስልት እንዲቀይሱ ያስገድዳቸዋል፡፡ጠንካራ የፖለቲካ ፓርቲ ጠንካራና ዘላቂ የገንዘብ ምንጭ ሊኖረው የግድ ነው፡፡

**ውድ የፕሮግራሙ ታዳሚዎች፤ ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ** በኢትዮጵያ ውስጥ ጠንካራ ተፎካካሪ የፖለቲካ ድርጅት ሆኖ ከላይ በከፊል የጠቃቀስናቸውን የህዝባችንን ሰቆቃዎች መፍታት ይችል ዘንድ የአባላቱ እና የገዳፊዎች እገዛ እጅግ አስፈላጊ ነው፡፡ ፓርታያችን ይዞ የታለሳቸውን ዓላማዎች እውን ለማድረግ ሁላችንም የምንችለውን ልናበረክት ይገባል፡፡

እያንዳንዳችን በሚልዮን የሚቀጠር ገንዘብ ብናዋጣ ላንጨርሰው የምንችለው ሰፊ ስራ ከፍታችን ይጠብቀናል፡፡ዛሬም ሆነ ወደፊት ለፓርቲያችን የምታደርጉት ድጋፍ ውጤታማ ፖሊሲዎችንና ፕሮግራሞችን በመቅረጽ የሀገራችንን ዘርፈ ብዙ ችግሮች ለመቅረፍ ቀጥተኛ አስተዋጾ እንዳለው ለማስታወስ እወዳለሁ፡፡ አንገታችንን የሚያሰደፋ የድህነትና የርሀብ ችግር ከሀገራችን ተወግዶ፣ አድሏዊ አሰራርና ኢ-ፍትሀዊነት በዴሞክራሲያዊ ስርአት ተተክቶ ለማየት ገንዘባችንን ብቻ ሳይሆን ከዚያም በላይ ያለንን ውድ ነገር ልናበረክት ይገባል፡፡ ጥቂቶችን ተጠቃሚ ለማድረግ ሆን ተብሎ የተቀረጹ ፖሊሲዎች ሰለባ የሆኑ የከተማ ድሆችን፣ አርብቶ አደር እና አርሶ አደር ህዝባችንን ለመታደግ ሳንሳ ልንደግፍ ይገባናል፡፡ **ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ** የህዝባችንን ሀዘን በደስታ፣ መድሎን በፍትህ፣ ጭቆናን በነጻነት፣ ጥላቻን በፍቅር የሚለውጥ ፓርቲ ይሆን ዘንድ ዛሬ ልንደግፈው ታሪካዊና የዜግነት ግዴታ አለብን፡፡

ለመጪው ትውልድ የተሻለች ሀገር ለማስረከብ እና ከታሪክ ተወቃሽነት ለመዳን የ**ነጻነትና እኩልነት ፓርቲን እንደግፍ፡፡**
**ነጻነት፣ እኩልነትና ፍትህ ለመላው የሀገራችን ህዝቦች፡፡**
**አመሰግናለሁ፡፡**